# የጉላፕ ዓይነቶች
## መስፍን አረጋ

"So easy it seems once found, yet when unfound most would have thought impossible."
ዮሐንስ ሚልተን (John Milton)

ከተገኘ በኋላ ቢመስልም በጣም ቀላል፣
ከመገኘቱ በፊት ይመስል ነበር የማይቻል።
መስፍን አረጋ

## መንደርደርያ

ይህ ጦማር (article) በጉላፕ ዓይነቶች (types of degrees) ላይ የሚያተኩር ጦማር ሲሆን፣ የሀርኪታ ዓይነቶች (types of schools) በሚል ርዕስ በቅርቡ የጦመርኩት ጦማር (http://www.ethiomedia.com/assert/types_of_schools.pdf) ተከታይ ጦማር ነዉ። እነዚህ ሁለት ጦማሮች ደግሞ «**ሰገላዊ አማረኛ**» (**አማሮምኛ**) በሚል ርዕስ በቅርቡ ካሳተምኩት መጽሐፍ የተቀነጨቡ ቅንጫቢወች ናቸዉ።

**ሰገል** ማለት በግእዝ ጥበብ ማለት ሲሆን፣ ሳይንስ የሚለዉን የባእድ ቃል ይተካልናል። ከዚህም **ሰገለኛ** (scientist)፣ **ሰገላዊ** (scientific) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን። ስለዚህም «**ሰገላዊ አማረኛ**» ማለት «ሳይንሳዊ አማረኛ» (Scientific Amharic) ማለት ይሆናል። «**አማሮምኛ**» ማለት ደግሞ አማረኛንና ኦሮምኛን በማጣመር የፈጠርኩት ቃል ነዉ፣ አማረኛን ሰገላዊ ለማድረግ የኦሮምኛን ቋንቋ በሰፊዉ ተጠቅሜበታለሁና፣ ለኦሮምኛ ቋንቋ ምስጋና ይግባዉና።

የ«ሰገላዊ አማረኛ» **ሁለተኛ ሰርሰም** (second edition) ተጽፎ የተጨረሰ ሲሆን አቅሙ ሲፈቅድልኝ ይታተማል። **ሰርሰም** (edition) ማለት ከዚህ ቀደም ለማርባት በማያመችና አሻሚ በሆነ ሁኔታ «እትም» እንለዉ የነበረዉ ሲሆን፣ ቃሉ የተገኘዉ ሲሬሱ (እርማት) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ነዉ። ግሱም ሲረባ **ሰረሰመ** (edit)፣ **ስርስም** (edited)፣ **ሰርሳሚ** (editor)፣ **ስርሰማ** (editing) እያለ ይሄዳል። ስለዚህም «**ሁለተኛ ሰርሰም**» (second edition) ማለት ከዚህ በፊት «ሁለተኛ እትም» እንለዉ የነበረዉ ነዉ ማለት ነዉ።

ይሄን ጦማሪ በጾዳቤ (email) «**mesfin.arega@gmail.com**» በመጾደብ ማግኘት ይቻላል። **ጾዳቤ** (email) ማለት ኢሜይል ማለት ሲሆን፣ ቃሉ የተገኘዉ ጾፓስ (electric) እና ደብዳቤ የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ነዉ። ግሱም ሲረባ ጾደበ (to email)፣ ጹድብ (emailed)፣ ጾዳቢ፣ ጹደባ (emailing) እያለ ይሄዳል። ጾፓስ (electric) የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ደግሞ ጦምፒስ (መብራት) ከሚለዉ የወላይትኛ ቃል ነዉ።

## የትምሕርት ዘርፎች

የትምሕርት ዘርፎች ኪንሰብ (arts)፣ ምንድሳ (engineering)፣ ሰገል (science) ተብለዉ በሶስት አብይ ዘርፎች ይከፈላሉ። ለምሳሌ ያህል ዱኛኪን (economics)፣ ታሪኪን (history)፣ ጹፍኪን (literature) የኪንሰብ ዘርፎች ናቸዉ፣ ቤታደር ምንደሳ (civil engineering)፣ ተልኑሲን (electronics)፣ ስየቃ (architecture) የኪንሲን ዘርፎች ናቸዉ፣ ጉሲን (physics)፣ ፓካርሲን (chemistry)፣ ሂወሲን (biology) ደግሞ የሰገል ዘርፎች ናቸዉ።

| የትምሕርት ዘርፎች | |
|---|---|
| ኪንሰብ | arts |
| ምንደሳ | engineering |
| ሰገል | science |

መሐንዲስ የሚለዉን ቃል ለማርባት ይመች ዘንድ ወደ መንዳሽ እንለዉጠዋለን:: ግሱም ሲረባ መነደሰ (to engineer)፣ ምንድስ (engineered)፣ መንዳሽ (engineer)፣ ምንደሳ (engineering) እያለ ይሄዳል::

## የትምሕርት ደረጃወች

አንድ ተማሪ ትምሕርቱን በስኬት ሲጨርስ ከተማረበት ሀርኪታ (school) ዳዉንቻ (certificate)፣ ደችሉክ (diploma) ወይም ጉላፐ (degree) ይቀበላል:: ጉላፖች ደግሞ ሲማክቶ (bachelor)፣ ሊቃቶ (masterate) እና ዲባቶ (doctorate) ተብለዉ በሶስት ደረጃወች ይመደባሉ::

| የትምሕርት ደረጃወች | | | |
|---|---|---|---|
| certificate | ዳዉንቻ | bachelor | ሲማክቶ (ሲ/ቶ) |
| diploma | ደችሉክ | masterate | ሊቃቶ (ሊ/ቶ) |
| degree | ጉላፐ | doctorate | ዲባቶ (ዲ/ቶ) |

ዳዉንቻ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ኦደንችቻ (አወራ፣ ተናገረ) ከሚለዉ የወላይትኛ ቃል ሲሆን፣ ግሱም ሲረባ ደወነቸ (certify)፣ ድዉንች (certified)፣ ደዉናች (certifier, certifying)፣ ድዉነቻ (certification) እያለ ይሄዳል:: ስለዚህም ተደዉናች (certifiable)፣ ደዉናች ወኪል (certifying agent)፣ ድዉንች ሚሻ (certified check) ይሆናሉ:: ሚሻ (check,cheque) የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ሚሸሻ (ገንዘብ) ከሚለዉ የወላይትኛ ቃል ነዉ::

ደችሉክ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ደቻሳ (የታጠፈ) የሚለዉን የኦሮምኛ ቃልና ሉክ የሚለዉን ያማረኛ ቃል በማጣመር ነዉ:: እግረመንገዳችንን ቶፍታ (ዘዴ) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ቶፍካ (diplomacy)፣ ቶፍከኛ (diplomat)፣ ቶፍካዊ (diplomatic)፣ ቶፍካሲን (diplomatics) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን::

ጉላፐ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ጎለመ (ከፈለ፣ ለየ) ከሚለዉ ያማረኛ ቃል ነዉ:: ለምሳሌ ያህል ሴልሽስ ጉላፐ (Celsius degree)፣ ፋረንሐይት ጉላፐ (Fharenheit degree)፣ የነጻነት ጉላፐ (degree of freedom) ይሆናሉ::

ሲማክቶ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ምስማክ (መሠረት፣ ድጋፍ፣ መጠጊያ) የሚለዉን የግእዝ ቃል አቶ ከሚለዉ ቃል ጋር በማጣመር፣ ሊቃቶ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ሊቀ (አለቃ) እና አቶ የሚሉትን ቃሎች በማጣመር፣ ዲባቶ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ደግሞ ዲበ (በላይ) የሚለዉን የግእዝ ቃል አቶ ከሚለዉ ቃል ጋር በማጣመር ነዉ::

### 1) የሲማክቶ ጉላፐ ዓይነቶች

ቫይካዲን (university) ዉስጥ የሚሰጥ የመጀመርያ ጉላፐ ሲማክቶ ጉላፐ (bachelor degree) ወይም ባጭሩ ሲጉ ይባላል:: ሲማክቶ ጉላፐ ያለዉ ሰዉ ስም ሲጻፍ ከስሙ በፊት ሲማክቶ (ሲ/ቶ) ሊጨመር ይችላል፣ ይገባልም፣ መከባበር ዋናዉ ባህላችን ነዉና:: ለምሳሌ ያህል «ሲማክቶ አማረ መስፍን» ወይም ባጭሩ «ሲ/ቶ አማረ መስፍን» ተብሎ ሊጻፍ ይችላል::

ሲማክቶ ጉላፐ በሰገል (science) መልክ ሲሰጥ ሲማክሲን ጉላፐ (bachelor of science degree) ወይም ባጭሩ ሲሲጉ (B.Sc.) ይባላል፣ በኪንሰብ (arts) መስክ ሲሰጥ ሲማኪን ጉላፐ (bachelor of arts degree) ወይም ባጭሩ ሲኪጉ (B.A) ይባላል፣ በሕግ (law) መስክ ሲሰጥ ሲማሕግ ጉላፐ (bachelor of law degree) ወይም ባጭሩ ሲሕጉ (Ll.B) ይባላል፣ በምንደሳ (engineering) መስክ ሲሰጥ ደግሞ ሲማንድ ጉላፐ (bachelor of engineering degree) ወይም ባጭሩ ሲማንጉ (B.Eng) ይባላል::

| የሲማክቶ ጉላፐ ዓይነቶች | |
|---|---|
| bachelor degree | ሲማክቶ ጉላፐ (ሲጉ) |
| bachelor of arts | ሲማኪን ጉላፐ (ሲኪጉ) |
| bachelor of engineering | ሲማንድ ጉላፐ (ሲማንጉ) |
| bachelor of law | ሲማሕግ ጉላፐ (ሲሕጉ) |
| bachelor of science | ሲማክሲን ጉላፐ (ሲሲጉ) |

**2) የሊቃቶ ጉላፐ ዓይነቶች**

ቫይካዲን (university) ዉስጥ የሚሰጥ ሁለተኛ ጉላፐ ሊቃቶ ጉላፐ (masterate degree, masters degree) ወይም ባጭሩ ሊጉ ይባላል:: ሊቃቶ ጉላፐ ያለዉ ሰዉ ስም ሲጻፍ ከስሙ በፊት ሊቃቶ (ሊ/ቶ) ሊጨመር ይችላል:: ለምሳሌ ያህል «ሊቃቶ አረጋ ወልደዮሐንስ» ወይም ባጭሩ «ሊ/ቶ አረጋ ወልደዮሐንስ» ተብሎ ሊጻፍ ይችላል::

ሊቃቶ ጉላፐ በሰገል መልክ ሲሰጥ ሊቀሲን ጉላፐ (master of science degree) ወይም ባጭሩ ሊሲጉ (M.Sc.) ይባላል፣ በኪንሰብ መስክ ሲሰጥ ሊቀኪን ጉላፐ (master of arts degree) ወይም ባጭሩ ሊኪጉ (M.A) ይባላል፣ በሕግ መስክ ሲሰጥ ሊቀሕግ ጉላፐ (master of law degree) ወይም ባጭሩ ሊሕጉ (Ll.M) ይባላል፣ በምንደሳ መስክ ሲሰጥ ደግሞ ሊማንድ ጉላፐ (master of engineering degree) ወይም ባጭሩ ሊማንጉ (M.Eng) ይባላል::

| የሊቃቶ ጉላፐ ዓይነቶች | |
|---|---|
| masterate degree | ሊቃቶ ጉላፐ (ሊጉ) |
| master of arts | ሊቀኪን ጉላፐ (ሊኪጉ) |
| master of engineering | ሊማንድ ጉላፐ (ሊማንጉ) |
| master of law | ሊቀሕግ ጉላፐ (ሊሕጉ) |
| master of science | ሊቀሲን ጉላፐ (ሊሲጉ) |

**3) የዲባቶ ጉላፐ ዓይነቶች**

ቫይካዲን ዉስጥ የሚሰጥ የመጨረሻ ጉላፐ ዲባቶ ጉላፐ (doctorate degree) ወይም ባጭሩ ዲጉ ይባላል:: ዲባቶ ጉላፐ ያለዉ ሰዉ ስም ሲጻፍ ከስሙ በፊት ዲባቶ (ዲ/ቶ) ሊጨመር ይችላል:: ለምሳሌ ያህል «ዲባቶ መስፍን አረጋ» ወይም ባጭሩ «ዲ/ቶ መስፍን አረጋ» ተብሎ ሊጻፍ ይችላል::

ዲባቶ ጉላፐ በሰገል መልክ ሲሰጥ ዲበሲን ጉላፐ (doctor of science) ወይም ባጭሩ ዲሲጉ ይባላል፣ በኪንሰብ መስክ ሲሰጥ ዲበኪን ጉላፐ (doctor of arts degree) ወይም ባጭሩ ዲኪጉ (D.A) ይባላል፣ በሕግ መስክ ሲሰጥ ዲበሕግ ጉላፐ (doctor of law degree) ወይም ባጭሩ ዲሕጉ (Ll.D) ይባላል፣ በምንደሳ መስክ ሲሰጥ ደግሞ ዲማንድ ጉላፐ (doctor of engineering degree) ወይም ባጭሩ ዲማንጉ (D.Eng) ይባላል::

በሰገል መስክ የሚሰጥ ዲባቶ ጉላፐ አብዛኛዉን ጊዜ የሚታወቀዉ **ፍልስፍና ዲባቶ**(doctor of philosophy) ወይም ባጭሩ **ፍዲ** (Ph.D) በሚል ስያሜ ነዉ:: እጩ ዲባቶ (Ph.D Candidate) ወይም ባጭሩ እዲ ማለት ደግሞ የዲባቶ ጉላፐ ገና ያለገኛ (ማለትም ለማግኘት እየሠራ ያለ) ማለት ነዉ::

| የዲባቶ ጉላፕ ዓይነቶች | |
|---|---|
| doctor | ዲባቶ |
| doctorate degree | ዲባቶ ጉላፕ (ዲጉ) |
| doctor of arts degree | ዲበኪን ጉላፕ (ዲኪጉ) |
| doctor of engineering degree | ዲማንድ ጉላፕ(ዲማንጉ) |
| doctor of law degree | ዲበሕግ ጉላፕ (ዲሕጉ) |
| doctor of science degree | ዲበሲን ጉላፕ (ደሲጉ) |
| doctor of philosophy | ፍልስፍና ዲባቶ (ፍዲ) |
| Ph.D Candidate | እጩ ዲባቶ (እዲ) |

## 4) የሕክምና ጉላፖችና ሌሎች ማዕረጎች

በሕክምና መስክ የሚሰጥ የመጀመርያ ጉላፕ፣ ቤንካ ጉላፕ (medical doctor) ወይም ባጭሩ ቤንጉ (MD) ሲባል፣ ባለጉላፑ ደግሞ ቤንካ (doctor) ይባላል፡፡ ቤንካ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ቤካ (የባህል መድሐኒት አዋቂ) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ነዉ፡፡ ቤንካ ጉላፕ ያለዉ ሰዉ ስም ሲጻፍ ከስሙ በፊት ቤንካ (ቤ/ካ) ሊጨመር ይችላል፣ ይገባልም፡፡ ለምሳሌ ያህል «ቤንካ መላኩ በያን» ወይም ባጭሩ «ቤ/ካ መላኩ በያን» ተብሎ ሊጻፍ ይችላል፡፡

በነገራችን ላይ **ቤንካ መላኩ በያን** በሕንድና በሕቡር አሜሪቃ ግዛቶች (United States of America) በመማር በዘመናዊዉ ትምሕርት የመጀመርያዉን የሚድካ ጉላፕ (college degree) ያገኙ ፣ በጣልያን ወረራ ጊዜ ላገራቸዉ ለጦቢያ ነጻነት ከወንድሞቻችን ከጥቁር አሜሪቃዉያን ጋር ከፍተኛ ቶፍካዊ (diplomatic) ተጋድሎ ያደረጉና፣ የጦቢያን የምርምር ምክርቤት (Ethiopian Research Council) የመሠረቱ ታላቅ ሰዉ ነበሩ፡፡ ባለመታደል ግን ምንም ላልፈየዱላት ባዕዳኖች ሐዉልቶችን ያቆመችዉ፣ አደባባዮችን የሰየመችዉ አገራችን፣ ለገዛ ራሷ ልጅ ለመላኩ በያን ግን አንድም መታሰቢያ አልሰየመችም፡፡ የራሷ አሮባት የሰዉ የምታማስል ያልታደለች ምስኪን አገር፡፡

ልዩ (special) ከሚለዉ ቃል ለየመ (specialize) የሚለዉን ግስ እናገኛለን፡፡ ግሱም ሲረባ ለየመ፣ ልይም (specialized)፣ ለያሚ (specializer, specialist)፣ ልየማ (specialization) እያለ ይሄዳል፡፡ ስለዚህም ልየማፍና (specialism) ይሆናል፡፡

ቤንካ ጉላፕ ያገኘ ሰዉ በልዩ በሽታ ሲለይም የሚያገኘዉ ጉላፕ፣ ዲቤንካ ጉላፕ ወይም ባጭሩ ዲቤንጉ ሲባል፣ ባለጉላፑ ደግሞ ዴበንጉ ወይም ለያሚ (specialist) ይባላል፡፡ ዲቤንካ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ዲባቶ እና ቤንካ የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ነዉ፡፡ ዲቤንካ ጉላፕ ያለዉ ሰዉ ስም ሲጻፍ ከስሙ በፊት ዲቤንካ (ዲ/ካ) ሊጨመር ይችላል፣ ይገባልም፡፡ ለምሳሌ ያህል «**ዲቤንካ አስራት ወልደየስ**» ወይም ባጭሩ «ዲ/ካ አስራት ወልደየስ» ተብሎ ሊጻፍ ይችላል፡፡

እግረመንገዳችንን ሐፀነ (ማቀፍ፣ ማጥባት፣ ልጅ ማሳደግ) ከሚለዉ የግእዝ ቃል፣ ፀናሚ (nurse) የሚለዉን ቃል እናገኛለን፡፡ ግሱም ሲረባ ፀነመ (to nurse)፣ ፅንም (nursed)፣ ፅናሚ፣ ፅነማ (nursing) እያለ ይሄዳል፡፡ ፅነማ ከሚለዉ ቃል፣ ፅነማ ሀርኪታ (nursing school)፣ ፅነማ ቤት (nursing home)፣ ፀኒምሻ (nursery) የሚሉትን እናገኛለን፡፡ ፀኒምሻ ማለት የሕጻናት ክፍል እንደ ማለት ነዉ፡፡ ፅነማ ሀርኪታ (nursing schoo) የሚለዉ ደግሞ ባጭሩ ፅናርኪታ ሊባል ይችላል፡፡

የፀናሚወች አለቃ ሴት ከሆነች ኦቢልት (sister) ስትባል፣ ወንድ ከሆነ ደግሞ ኦቢል ይባላል፡፡ ኦቢልት የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ኦቦሌቲ (እህት) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ነዉ፡፡ የኦቢልት ስም ሲጻፍ ከስሙ በፊት ኦቢልት ወይም ባጭሩ ኦ/ት ሊጨመር ይገባል፡፡ ለምሳሌ ያህል «ኦቢልት ዙርያሽወርቅ አረጋ» ወይም «ኦ/ት ዙርያሽወርቅ አረጋ» ተብሎ ሊጻፍ ይችላል፡፡ የኦቢል ስም ስጻፍ ደግሞ ከስሙ በፊት ኦቢል ወይም ባጭሩ ኦ/ቢ ሊጨመር ይገባል፡፡ «**ኦቢልት ዙርያሽወርቅ አረጋ**» በፀናሚነት ሕሙማንን በቅን ታገለግል የነበረች፣ በወጣትነቷ የተቀጨች ታላቅ እህቴ ናት፡፡

| የሕክምና ጉላፖችና ሌሎች ማዕረጎች | |
|---|---|
| doctor of medicine | ቤንካ |
| specialist | ለያሚ፣ ዲቤንካ |
| nurse | ፀናሚ |
| head nurse (female), sister | ኦቢልት (ኦ/ት) |
| head nurse (male) | ኦቢል (ኦ/ል) |
| nursing school | ፅነማ ሀርኪታ (ፅናርኪታ) |

«ቤት ወጌሻ» የሚለዉን ሐረግ በማሳጠር ቤግሻ (clinic)፣ ቤግሻዊ (clinical)፣ ቤግሸኛ (clinician)፣ ቤግሻ (ዊ) ሙቀትለኪ (clinical thermometer) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን።

ሥራሥር (መዳኒት) ከሚለዉ ቃል ሠሥር (pharmacy)፣ ሠሥረኛ (pharmacist)፣ ሠሥራዊ፣ ሠሥረኛዊ (pharmaceutic, pharmaceutical)፣ ሠሥርሲን (pharmacology, pharmaceutics)፣ ሠሥርሲነኛ (pharmacologist)፣ ሠሥርሲናዊ (pharmacological) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን።

ሆምኪታ (hospital) ማለት ሐኪምቤት (ሆስፒታል) ማለት ሲሆን፣ ቃሉ የተገኘ ዉም «ሕሙማን» ከሚለዉ ያማረኛ ቃልና ኪታ (ቤት) ከሚለዉ የወላይትኛ ቃል ነዉ። ግሱም ሲረባ ሆመከተ (hospitalizስ)፣ ሁምክት (hospitalized)፣ ሆምካች (hospitalizing, hospitalizer)፣ ሁምከታ (hospitalization) እያለ ይሄዳል። ሆምኪተኛ (hospital worker) ማለት ደግሞ የሆምኪታ ሠራተኛ ማለት ነዉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| pharmacy | ሠሥር | pharmacist | ሠሥረኛ |
| clinic | ቤግሻ | clinician | ቤግሸኛ |
| hospital | ሆምኪታ | hospital (worker) | ሆምኪተኛ |

ስላነበቡኝ አኮቴ (thanks)። በሌላ ጦማር (article) እስከምንገኛኝ ድረስ ደህና ይሰንብቱ፣ አብሔር (God) - የጦቢያ አምላክ - ይጠብቅወ።

መስፍን አረጋ ዘብሔረ ኩሽ
የትብቱ ቀብር ደሴ፣ ሳላይሽ።
mesfin.arega@gmail.com